| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምዳዊ ፡ ጽሑፍ ፤ "መሥራች ፡ ጽሑፍ ። " |
| ርእስ ፤ | "የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፦ ሥልጡንሕዝብና ። ሥልጡንሕዝብና ፡ በማክዳ ፡ ንግሥና ። " |
| ደራሲ ፤ | ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ። |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 1989 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2012-001 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | (ከ23 ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፥ ዳግመኛ ፡ የወጣ ። ) |

# መሥራች ፡ ጽሑፍ ።

founding article | article fondateur | مقالة تأسيسية

# የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፦ ሥልጡንሕዝብና ።

## ሥልጡንሕዝብና ፡ በማክዳ ፡ ንግሥና ።

ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ።

---

[ሥልጡንሕዝብና ፥ 7ኛ ፡ ዓመት ፥ ቍ.008 ፥ መስከረም ፡ 1989 ፡ ዓ.ም. ። ]

ማክዳ ፥ በአጋቦስ ፡ ሥርወ ፡ ንጉሥ ፡ ተራ ፡ ላይ ፡ 74ኛዋ ፡ ኾና ፥ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ ወሳባ ፡ ተብላ ፡ በቀኑንሽርናዋ ፡ ነገሠች ። ርሷም ፥ በዝሮዋ ፡ የምትሰማውን ፡ የንጉሥ ፡ ሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፡ በዐይኗ ፡ ለማየት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በኼደችበት ፡ ጊዜ ፥ ንጉሡ ፡ ለክብሯ ፡ ካገባው ፡ ግብር ፡ በኋላ ፥ ወደ ፡ ማረፊያዋ ፡ ልትኼድ ፡ ስትነሣ ፥ "ከመሸ ፡ የት ፡ ትኼጃለሽ ፡ እዚህ ፡ ዕደሪ ፡ እንጂ" ፡ ሲላት ፤ "አላደርም ፤ ኋላ ፡ ከክብሬ ፡ ያሳነስኸኝ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ሕዝቤ ፡ ካልጋ ፡ ያወርደኛል" ፡ ያለችው ፡ መሠረተ ፡ ነገር ፡ ይታወሳል ። እየተናገርነው ፡ እንደመጣነው ፡ ኾሉ ፥ ከጥንት ፡ አንሥቶ ፥ በአቢስያ ፡ ንጉሥን ፡ ሠያሚውና ፡ ሻሪው ፣ ጌታው ፡ ሕዝቡ ፡ እንደነበረ ፡ ያረጋግጣል ። "የፈሩት ፡ ይደርሳል ፤ የጠሉት ፡ ይወርሳል" ፡ ነው ። የፈራችው ፡ አልቀረም ፤ ደረሰ ። በዚያች ፡ ዕለት ፥ ከንጉሡ ፡ ምንይልክን ፡ ፀንሳ ፡ ኖሮ ፥ ተመልሳ ፡ አገሯ ፡ ስትገባ ፥ ዐንሰባ ፥ ልዩ ፡ ስሙ ፡ ማይበላ ፡ (አስመራ) ፡ እተባለው ፡ ስፍራ ፡ ስትደርስ ፥ ምንይልክን ፡ ወለደች ። "ንግሥተ ፡ አዜብ ፥ በእግዚአብሔር ፡ አምና ፥ ከንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ ወልዳ ፡ መጣች" ፡ ማለትን ፡ ያኰስም ፡ ሽማግሌዎች ፡ (አገር ፡ የቀሩት ፡ ያ̊ባት ፡ አባላት) ፡ ሲሰሙ ፥ "የአጋቦስን ፡ አምላክ ፡ ፀሓይን ፡ ክደሽ ፣ ሌላን ፡ አምልከሽ ፥ ከንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ ወልደሽ ፣ የአጋቦስን ፡ ዘር ፡ ለውጠሽ ፥ ተመልሰሽ ፡ እኛ ፡ ከተማ ፡ አትገቢም ፤ አጋቦስ ፡ ዐልጋ ፡ ላይ ፡ አትቀመጪም" ፡ ብለው ፡ ሊከለክሏት ፡ ተነሣሥተው ፡ ነበር ። ተከትለዋት ፡ የኼዱና ፡ ተከትለዋት ፡ የመጡ ፡ የአ̊ባት ፡ ሽማግሌዎች ፥ "ሃይማኖቷን ፡ የለወጠችው ፡ በፍጡሯ ፡ ፀሓይ ፡ ፈጣሪዋን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ዐውቃ ፥ ልጅ ፡ የወለደችውም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ዐድራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ ከቶ ፡ በራሷ ፡ አዶለም" ፡ ብለው ፡ ሲነግሯቸው ፥ ተረዱ ። ፀሓይን ፡ በማመን ፡ የፈጣሪዋን ፡ መብት ፡ ዐወቁ ፤ ንግሥታቸውን ፡ ተቀበሉ ። ንግሥት ፡ ማክዳ ፥ ልጇን ፡ ምንይልክን ፡ ታቅፋ ፥ አኵስም ፡ ቤተ ፡ መንግሥቷ ፡ በክብር ፡ በደስታ ፡ በእልልታ ፡ ገባች ።

አቤቶ ፡ ምንይልክ ፥ አባቱን ፡ ንጉሥ ፡ ሰሎሞንን ፡ ለማየትና ፡ ጥበቡን ፡ ለመቅሠም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወርዶ ፥ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ቈይቶ ፤ አባቱ ፡ "ንጉሠ ፡ ጽዮን" ፡ ብሎ ፡ ሠይሞት ፥ ወደ ፡ አገሩ ፡ ሲመለስ ፥ ጽላተ ፡ ሙሴንና ፡ አብኳር ፡ እስራኤላውያንን ፡ አስከትሎ ፡ ቢመጣ ፥ የሕዝብን ፡ መብት ፡ የምትጠነቅቅ ፡ ንግሥት ፡ ማክዳ ፥ እንግዶቹን ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተቀብላ ፥ ለእያንዳንዳቸው ፡ የዕርሻ ፡ ምድር ፣ የከተማ ፡ ቦታና ፡ የመቃብር ፡ መሬት ፡ ተክላ ፥ ባንድ ፡ ወገን ፡ በጭቃ ፡ ልደት ፥ በሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ በምንይልክ ፡ ወላጅነት ፥ ከአበሻ [1] ፡ እና ፡ ሐበሻት [2] ፡ ጋራ ፡ በሥጋ ፡ ልደት ፡ አስተካክላ ፥ በሀገሬነት ፡ ሠራቻቸው ። በእኩል ፡ እግዚእነትና ፡ በእኩል ፡ ዜግነት ፥ ሿሚ ፣ ሻሪ ፣ ሐራ ፡ አካልነት ፡ ባንድ ፡ ሕዝብና ፡ አዋሐደቻቸው ። ጽላተ ፡ ሙሴን ፡ በመኣ ፡ ሀገሪቱ ፣ ለመኣ ፡ ሀገሪቱ ፡ ጕልት ፡ ተክላ ፥ የሕዝቧ ፡ ውሕደት ፡ የጸናባትን ፡ የብጤን ፡ መብትና ፡ ነጻነት ፡ በማክበር ፡ ወንፈል ፥ የራስን ፡ ማስከበር ፡ የምትለውን ፡ ኹለት ፡ ፊት ፡ ርትዕ ፥ በላይ ፡ የፈጣሪን ፥ በታችም ፡ የንጉሥን ፡ ፈንታ ፡ አጕልታ ፡

---

1 አበሻ ፤ የኵሽ ፡ ልጅ ፡ የአቢስ ፡ ዘሮች ፤ የኢትዮጵያ ፡ መደባይ ፡ ሕዝብ ። [አዘጋጅ]

2 ሐበሻት ፤ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፥ ከመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ተሰደው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተሻገሩ ፡ ሴማውያን ፡ ነገዶች ። [አዘጋጅ]


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።

በማከል ፥ ባራት ፡ ፊት ፡ አስፋፍታ ፡ ፍጹም ፡ ብሔራዊት ፡ አደረገቻት ። ኀቡኡን ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈንታ ፡ ለሚመለከተው ፡ ተወላጅ ፡ ልቦና ፡ ስትተው ፥ ከፈጻሚው ፡ ሥልጣን ፡ ጋራ ፡ ተዳብሎ ፡ በገቢር ፡ የኖረውን ፥ ፈታሒውን ፡ ሥልጣን ፡ ለይታ ፡ አውጥታ ፥ ከቀሩት ፡ በመብት ፡ አስተካክላ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ሐቅ ፥ ፍርድን ፡ ለሚጠብቀው ፡ ለምሁሩ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ በመስጠት ፥ ዐልጋዋን ፡ በኀላፊነት ፡ ተለያይተው ፥ በሥልጣን ፡ በተመዛዘኑ ፡ ሦስት ፡ ደንቦች (3) ፡ ዛኅን ፡ ላይ ፡ አዝንታ ፡ ዘረጋች ። ፍትሕን ፡ ነጻ ፡ አወጣች ። ባለፈው ፡ *ሥልጡንሕዝብና* ፡ አንቀጽ ፡ ቍ.006 ፡ እንዳነበብነው ፥ ከጥንት ፡ አንሥቶ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ በመጣው ፡ የአበሳንያ ፡ ሥርዐት ፥ ንጉሥ ፡ ያነገሠውን ፡ ሕዝብ ፡ ለመግዛት ፡ መብት ፡ ሲኖረው ፥ ያላነገሠውን ፡ ለመግዛት ፡ አይችልም ፡ ነበርና ፥ ንግሥት ፡ ማክዳ ፥ እስራኤላውያንን ፡ ሢሶ ፡ አካል ፡ ያዋሐደውን ፡ ዐዲስ ፡ ሕዝብ ፡ ለመግዛት ፡ የማይገባት ፡ መኾኗን ፡ አስታወቀች ። በርሱ ፡ ላይ ፡ ባዲስ ፡ ለመሠየምም ፡ ከርሷ ፡ ይልቅ ፡ የሚገባው ፥ ኹሉ ፡ እኩል ፡ የሚወለዱትና ፡ ዜጋው ፡ የኾኑለት ፡ ልጇ ፡ ንጉሥ ፡ ምንይልክ ፡ መኾኑን ፡ አረጋግጣ ፥ ርሱን ፡ በመብቱ ፡ ለማንገሥ ፥ ርሷ ፡ በፈቃዷ ፡ ሠያሚት ፡ የሕዝብ ፡ አባል ፡ ኾነች ።

በእስራኤላውያን ፡ ሢሶ ፡ አካልነት ፥ ባንድ ፡ የበየደችውን ፡ እግዚእ ፣ ሐራ ፡ ሕዝብ ፥ በነገድ ፡ አባቶቹ ፥ ማለት ፥ በመንግሥቷ ፡ ዐዳ ፡ አጠቃላ ፡ ይዛ ፥ ባንድነቱ ፡ ኹለት ፡ ሕዝቦችን ፡ ያዛመደ ፥ ኹለት ፡ ዘውዶችን ፡ ያዋሐደ ፥ የኹለት ፡ ነገሥት ፡ ዘር ፡ የኾነ ፡ ልጇን ፡ ንጉሥ ፡ ምንይልክን ፡ የአጋቦስ ፡ ወሰሎሞናዊ ፡ ሥርወ ፡ ነገሥት ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥ ፈንታዋን ፡ ንግሥቱ ፡ ስታነግሠው ፥ ሥያሜው ፡ *"ንጉሠ ፡ ነገሥት"* ፡ እንዲባል ፡ ኹኔታው ፡ አስገደደ ። ማዕርጉም ፡ ተራውን ፡ መርበቢያ ፡ የነገሥታት ፡ መደብ ፡ እንዲኖረው ፡ አሳስቦ ፥ ርሱን ፡ ቀዳማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዐፄ ፡ ምንይልክ ፡ አሠኝታ ፥ እንዳባቶቹ ፡ ነገሥተ ፡ አቢሳን ፡ ኹሉ ፥ በመስከረም ፡ መባቻ ፡ 930 ፡ ቅድመ ፡ ልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ ግድም ፥ በሀገራዊ ፡ ወግ ፣ በደመቀ ፡ ከብካብ ፡ አነገሠችው ። ርሱም ፡ ፈንታውን ፥ ሥልጣኑ ፡ ለኹሉም ፡ የሚረብበትን ፡ መደቡን ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፥ በበታቹ ፡ የሚኾኑ ፡ 15 ፡ ንጉሦችን ፡ ባ 15 ፡ ክፍላተ ፡ ሀገር ፡ አነገሠ ።

በዚህች ፡ ብፅዕናዋ ፡ በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አንደበት ፡ የተመሰከረላት ፡ ቅድስት ፡ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ ማክዳ ፡ (ማቴ. ፡ ፲፪ ፣ ፵፪ ፤ ሉቃ. ፡ ፲፩ ፣ ፴፩) ፡ ሥልጡን ፡ ድርጊት ፥ ለገነቲቱ ፡ ሀገረ ፡ ኵሽ ፡ ወይም ፡ አበሳንያ ፦

ሀ) የመድረሻው ፡ ሥልጡንሕዝብና ፥ ባንድ ፡ በኩል ፡ በብጤ ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፤ በሌላው ፡ በኩል ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፍራቻና ፡ በሕግ ፡ አክብሮት ፡ ተመዛዛኝነት ፥ ባራት ፡ ማእዘን ፡ በተንሳተተ ፡ ዛኅን ፡ ላይ ፡ ለመቼውም ፡ ተስፋፍቶ ፡ ተዘረጋ ፤

ለ) የሕዝቧ ፡ መባረዝ ፡ በሦስት ፡ ዐበይት ፡ አንጋድ ፡ አካል ፡ ተከሥቶና ፥ በጊዜው ፡ በነበሩት ፡ ታናናሽ ፡ ኀብረቶች ፡ ወይም ፡ ዓሌቶች ፥ አንድም ፡ ሳይቀርላቸው ፡ ተሟልቶ ፥ እግዚእ ፣ ሿሚ ፣ ሻሪ ፣ አንድ ፡ ሐራ ፡ ሕዝብ ፡ ኾኖ ፡ በግብር ፡ ተወለደ ፤

ሐ) አንድነቱ ፡ የሞላው ፡ ሕዝብ ፡ የኾነ ፤ ሞላው ፡ ሕዝብ ፡ ያንድነቱ ፡ የኾኑለት ፤ በመንግሥቱ ፡ ባላንጣ ፡ የሌለበት ፤ ሥልጣኑ ፡ ድንት ፡ የሚኖር ፡ የሕዝብ ፡ ልጅ ፥ የኹለት ፡ ነገሥታት ፡ አንድ ፡ ዘርዐ ፡ ነገሥት ፡ በመብት ፡ ተወለደ ፤

መ) ቀዳሚው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ *"ርእስ"* ፥ በርትዕ ፣ ለርትዕ ፡ ተግባር ፥ በሕዝብ ፡ ተሠየመ ፤ ዘውዱ ፡ ተበጀ ፤ መብቱን ፡ አሟልቶ ፡ የተወለደው ፡ ቀዳማዊ ፡ ምንይልክ ፡ በሥልጡንሕዝባዊ ፡ ሥርዐት ፡ በመዠመሪያ ፡ ተቀዳጀው ፤

ሠ) ይህ ፡ ደገኛ ፡ ጠቅላላ ፡ ግብር ፥ ከዕለቱ ፡ አንሥቶ ፥ *"ሕዝብ ፡ አንጋሽ ፥ ንጉሥ ፡ ነጋሽ ፥ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ክርስቲያን) ፡ ቀዳሽ"* ፡ ለሚለው ፡ የሥልጣን ፡ ክፍያ ፡ የማይናወጥ ፡ የርትዕ ፡ መሠረትን ፡ ኾነ ።

*(ይቀጥላል ። )*

---

3 **ፈጻሚው** ፡ ሥልጣን ፣ **ፈታሒው** ፡ ሥልጣንና ፣ **ሐጋጊው** ፡ ሥልጣን ። [አዘጋጅ]


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።